ብልፅግና ፓርቲ
PROSPERITY PARTY

# “ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!”

# የብልጽግና ፓርቲ
# የአመራርና አባላት የዲስፐሊን መመሪያ

(*በማዕከላዊ ኮሚቴ የጸደቀ*)

በ5ኛው

የጋራ የምክክር መድረክ

የቀረበ

ጥር 27/2016 ዓ.ም.

ጅግጅጋ

# ከገለጻው የሚጠበቅ ውጤት

❖ ተሳታፊው:-

1. የፓርቲ አባልና አመራር ሊከተል የሚገባ የስነምግባር መርሆዎች/ህጎች በሚገባ ይገነዘባል፣
2. የስነ-ምግባር ጥሰቶችና ሊወሰዱ የሚችሉ ርምጃዎችን ይገነዛባል፣
3. *የቅሬታና የአቤቱታ የአሰራር ሥርዓት* ያውቃል፡፡
4. ትላትን ለተነሱ ጥያቄዎች(*የጊዜ ገደብ፣ ይግባኝ፣ የኮሚሽን ውሳኔ ተቀባይነት ካላገኘስ፣ ይርጋ እና ግንዛቤ*) ተገቢውን ምላሽ ያገኛል፡፡
5. በአጠቃላይ አውቆ ለማሳወቅ የሚያስችለው ትጥቅ ያገኛል፡፡

# የመመሪያው ህጋዊ መሰረት

1) መተዳደሪያ ደንብ
አንቀጽ 13(1)(1.10)

2) መተዳደሪያ ደንብ
አንቀጽ 23(6)(ረ)

3) መተዳደሪያ ደንብ
አንቀጽ 40

# የመመሪያው ይዘት


ክፍል 1
ጠቅላላ ድንጋጌ(1-4)

ክፍል 2
የአባላት ሥነ ምግባር መርሆዎች(5-6)

ክፍል 3
የሥነ-ምግባር የግንኙነት አግባቦች(7-13)

ክፍል 4
የሥነ-ምግባር ጥሰቶችና የእርምጃ አወሳሰድ(14-24)

ክፍል 5
የቅሬታና አቤቱታ አቀራረብና አፈታት የአሰራር ስርዓት(25-31

ክፍል 6
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች(32-38)




*"ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!"*

# ክፍል 1፡ ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. በመልካም የፓርቲ ስነ-ምግባር ለመመራት፣

2. የውስጠ ዴሞክራሲ ጥንካሬ እንዲኖረው ለማስቻል፣



3. የእርምት እርምጃ የሚወሰድበት ግልጽ አሰራር ለመዘርጋት

4. በጥሩ ተምሳሌት የሚጠራ አመራርና አባል በመፍጠር የፓርቲውን ህዝባዊ ቅቡልነት ማሳደግ ነው፡፡

አንቀጽ 3- ዓላማ

"ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!"

# አንቀጽ 2፣ ትርጓሜ

- በደንብ መነበብ የሚገባቸው፡-

9) "መልካም የፓርቲ ስነ-ምግባር"፣

10) "የስነ-ምግባር ጥፋት"፣

11) "የፖለቲካ ጥራት"፣

12) "ሙስና"፣

13) "መርህ አልባ ግንኙነት"

14) "ያልተገባ የጥቅም ትስስር"፣

15) "ሙስናን መዋጋት"፡፡

# አንቀጽ 4 - የተፈጻሚነት ወሰን

የፓርቲ መዋቅር፣

የፓርቲ አመራር፣

የፓርቲ አባላት፡፡

"ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!"

# ክፍል 2፡ የአባላት ሥነ ምግባር መርሆዎች

## አንቀጽ 5- መርሆዎች

1. እውነተኛነት፣
2. የሕዝቦችና የፓርቲው የወል እውነት፣
3. ዴሞክራሲያዊነት፣
4. የውስጠ ፓርቲ አንድነት፣
5. የህግ የበላይነት፣
6. ተጠያቂነት፣
7. ሚዛናዊነት፣

*"ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!"*

# አንቀጽ 6፡ የአባላትና አመራር የሥነ-ምግባር ግዴታዎች(#6)

1. ማንኛውም የፓርቲ አመራርና አባላት ህጎችና አሰራሮች የማክበር ግዴታ፤

2) የውስጠ ፓርቲ ዴሞክራሲን የማጠናከር ግዴታ፤

3) የፓርቲውን ውስጣዊ አንድነት፣ ጥራትና ጥንካሬ የመጠበቅ ግዴታ፤



4) የፓርቲውን እና የመንግስት ሚስጥር የመጠበቅ ግዴታ፤

5) ሙስና፣ ብልሹና አድሏዊ አሰራሮችን የመታገል ግዴታ እና

6) ፓርቲውን ሳይለቅ የሌላ የፖለቲካ ፓርቲ አባል መሆን ክልክል ነው፡፡

*"ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!"*

## (1) ማንኛውም የፓርቲ አመራርና አባላት የማክበር ግዴታ ያለበት ህጎችና አሰራሮች

1. ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ እና የአሰራር መመሪያዎችን  የማክበር፣
2. መርሆዎች፣ እሴቶችን ፣ ዉሳኔዎችን የማክበር፣
3. የህዝቡንና የሀገርን ደህንነትና ሉአላዊነትን የመጠበቅ፣
4. የሀገሪቱን ህጎችንና መንግስታዊ ውሳኔዎችን የማክበር፣ ማስከበር፣
5. የህግ የበላይነትን በማክበርና ማስከበር፣
6. የህብረተሰቡን መልካም እሴቶች የማክበርና  እንደ መጥፎ ስነ-ምግባር ከሚቆጠሩ የስነ-ምግባር ድርጊቶች እራስን የመቆጠብ፡፡

*“ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!”*

## (2) የውስጠ ፓርቲ ዴሞክራሲን የማጠናከር ግዴታ፡-

1. ለአባላት የተሰጡ መብቶች በተሟላ ሁኔታ የማክበርና የማስከበር፣
2. በማንኛውም የፓርቲ ስራዎችና እንቅስቃሴዎች የአባላትን ተሳትፎ የማረጋገጥ፣
3. በየደረጃው ባሉ የፓርቲ መዋቅሮች ሃሳባቸውን በቃልም ሆነ በጽሁፍ የማቅረብ መብታቸውን የማክበር፣
4. ስለፓርቲው ማወቅ፣ የመጠየቅና መልስ የማግኘት መብታቸውን የማክበር፣
5. የፓርቲውን ዶክመንቶች ለአባላት ተደራሽ የማድረግ፣
6. አሳታፊና ግልጽ ውይይትና የክርክር መድረኮችን በቀጣይነት መፍጠር፣
7. የእርስ በእርስ ግንኙነቶች በመተባበር፣ በመከባበርና በመቻቻል ላይ የተመሰረቱ ማድረግና ልዩነቶችና ግጭቶች በውይይትና በዴሞክራሲያዊ ትግል እንዲፈቱ ማስቻል፣
8. ሂስ በማቅረባቸው፣ በመታገላቸውና በመሰል ሁኔታዎች የቂም በቀል ድርጊት እንዳይፈጸም መታገል፡፡

## (3) የፓርቲውን ውስጣዊ አንድነት፣ ጥራትና ጥንካሬ የመጠበቅ

1. የፓርቲውን የፖለቲካ እሳቤዎች በብቃት የመገንዘብ፣ ለሌሎች የማስገንዘብና የተዛቡ አመለካከቶችን በዴሞክራሲያዊ መንገድ የመታገል፣
2. የፓርቲውን ውስጣዊ አንድነት፣ጥራትና ጥንካሬ የሚጎዱ ማናቸውንም ዝንባሌዎችና ድርጊቶችን የማጋለጥና የመታገል፣
3. በአባላት መካከል የሚኖርን መልካም ግንኙነት ከሚያጎድፉ ድርጊቶች የመቆጠብ፣
4. የራስን ድክመት በቅንነት የማረምና የሌሎች ድክመት እንዲታረም በዴሞክራሲያዊ መንገድ የመታገል፣
5. እውቀትና ክህሎት ለሌሎች የማስተላለፍና ከሌሎች ለመማር ዝግጁ የመሆን፣
6. ስራንና ተግባርን ማእከል ያደረገ ግምገማ እና ምዘና በማካሄድ ጥንካሬዎችን አጠናክሮ ማስቀጠልና ድክመቶችን ማረም፣
7. ከቡድንተኝነትና አንጃነት ራስን የመጠበቅና ሌሎችን የመታገል፣
8. የፓርቲ አባልነት መዋጮ በወቅቱ የመክፈል፡፡

## (4) የፓርቲውን እና የመንግስት ሚስጥር ስለመጠበቅ

1. ሚስጥራዊ ሰነዶች፣ ዶክመንቶች እና ጉዳዮችን በአግባቡ የመያዝ፣

2. በተለያዩ ውይይቶችና ስብሰባዎች የሚተላለፉ ውሳኔዎችን ከሚመለከተው አካል ውጭ ለሌላ አካል ማሳወቅ አይቻልም፤

3. በሚስጥር መያዝ አለባቸው የተባሉ ጉዳዮችን ወደ ውጭ ማውጣት የተከለከለ ነው፡፡

*“ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!”*

## (5) ሙስና፣ ብልሹና አድሏዊ አሰራሮችን የመታገል

1. የፓርቲና የመንግስት ገንዘብና ንብረት የመጠበቅና ለእራስ ጥቅም ያለማዋል፣

2. እራስን ከሙስናና ከብልሹ አሰራሮችና ድርጊቶች የመጠበቅና ሌሎችን የመታገል፣

3. አድሏዊ አገልግሎቶችና ውሳኔዎች ከመስጠት እራስን የመጠበቅና ሌሎችን የመታገል፣

4. የሃሰት ሪፖርት ያለማቅረብና የቀረቡለትን ሪፖርቶች ትክክለኛነት የመከታተልና የማረጋገጥ፣

5. በሃሰተኛ መረጃ በመመስረት ቅሬታና አቤቱታ ያለማቅረብ እና ሌሎችን በሃሰት ያለመወንጀል፣

6. የፓርቲ ሚስጥሮችን አሳልፎ ከመስጠት እራስን የመጠበቅና ሌሎችን የመታገል፣

7. ትክክለኛ ባልሆነ መረጃ በመመስረት የአባላት ምልመላ ማካሄድ፣ ህግና አሰራርን ሳይከተል የአባልና የአመራር ምደባና ስምሪት ከመስጠት እራስን የመጠበቅና ሌሎችን የመታገል፣

## 6) ፓርቲውን ሳይለቅ የሌላ የፖለቲካ ፓርቲ አባል መሆን ክልክል

1. በብልጽግና ፓርቲ አባልነት እያለ የሌላ ፓለቲካ ፓርቲ አባል ክልክል ስለመሆኑ፤

2. ከፓርቲያችን አቋሞች ጋር በሚፃረር መልኩ የሌሎች ፖለቲካ ፓርቲዎችን አቋም የማራመድም ሆነ የመደገፍ አዝማሚያዎችን ማሳየት የተከለከለ ነው፡፡

*“ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!”*

# ክፍል 3፡ የሥነ-ምግባር የግንኙነት አግባቦች(#7-13)

(1) በፓርቲው አባላትና አመራር መካከል

(2) በመንግስት ስራ ላይ

(3) ከህዝብ እና ከሲቪል ማህበራት ጋር

4) ከግል ዘርፍ/ባለሀብት ጋር



(5) ከተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር


(6) የህግ የበላይነትን ከማስከበር አኳያ

(7) የኮሙዩኒኬሽንና የሚዲያ አጠቃቀም

*"ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!"*

ብልፅግና ፓርቲ
PROSPERITY PARTY

# (7) በፓርቲው አባላትና አመራር መካከል ሊኖር የሚገባ ግንኙነት




1. የሰው ልጅ ሁሉ እኩል መሆኑን መቀበል፣
2. ለሌላው በወንድማማችነትና እህትማማችነት እሴት ላይ የተመሰረተ አክብሮት፣
3. በግልጽ መነጋገርን፣ መረዳዳትን፣ መማማርን፣ መደጋገፍን፣ መተባባርን፣ መተማመን፣ መከባበርንና መርህን በጠበቀ መልኩ ለፓርቲው ዓላማ በጋራ መሰለፍን ማዕከል ያደረገ ግንኙነት፣
4. ስልጣንን አላግባብ በመጠቀም የግል ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ጫና በአባል ላይ ከመፍጠር መቆጠብ
5. የኢትዮጵያዊ ባህሎችና እሴቶች በሚያዙት መሰረት ማህበራዊ ትስስሮችን መፍጠር፤
6. ከሀሜት፣ አሉባልታና በጥርጣሬ ላይ ተመስርቶ ስም ከማጥፋት መቆጠብ፣
7. ከፓርቲው አሰራር በተቃረነ መልኩ ተሰማርቶ የተገኘ አባል/አመራር የማረም ሃላፊነት፡፡

# (8) በመንግስት ስራ ላይ ስለሚኖር ግንኙነት፤

1. ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና እቅዶችን ከፓርቲያችን ፕሮግራም ጋር በተጣጣመ መልኩ መተግበር፣

2. የመንግስት ተቋማት ነፃ፣ ገለልተኛ እና ሙያዊ ብቃት ያላቸው መገንባት፣

3. የመንግስት እና የፓርቲ አሰራሮች መደበላለቅ የማስወገድ፣

4. እርስ በርስ የመተጋገዝ፣ የመተባበር እና ልምድ በመለዋወጥ ብቃት የማሳደግ ኃላፊነት

5. ከአመራሩ ጋር ለጋራ ዓላማ በትብብር የመስራት እና የፓርቲውን መርሆዎችና እሴቶች መላበስ፣

6. ከሥራ መቅረትም ሆነ ማርፈድ፣ ተጠሪ ከሆኑለት አካል ወይም የግድ መገኘት ባለባቸው መድረክ ከአዘጋጁ አካል ፍቃድ ሳያገኙ መቅረትም ሆነ ማርፈድ ተጠያቂ ያደርጋል፡፡

*"ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!"*

# (9) ከህዝብ እና ከሲቪል ማህበራት ጋር የሚኖር ግንኙነት

1. ህዝቡን በዕቅዶቻችንና በአፈጻጸሞቻችን ላይ ግልጽነት ባለው መልኩ ማሳተፍ፤

2. የልማት ስራዎቻችን ሰው ተኮር መሆናቸውን በተግባር ማረጋገጥ፤

3. አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

4. ከሲቪል ማህበራት ጋር ተቀራርቦ የመስራት፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚ ልማት ሥራዎች የማሳተፍ እና ህግና ሥርዓትን አክብረው እንዲሰሩ ማድረግ፡፡

*"ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!"*

# (10) ከግል ዘርፍ/ባለሀብት ጋር ሊኖር የሚገባ ግንኙነት

1. በኢኮኖሚ ውስጥ ዋናኛ ተዋናይ መሆናቸውን የመረዳትና ለተግባራዊነቱ መርህን በጠበቀ መልኩ የድርሻውን የመወጣት፣

2. የግል ዘርፉ ጤናማና ተወዳዳሪ እንዲሆን ግልፅነትና ተጠያቂነት ባለው አሰራር የመደገፍ እና ምቹ ሁኔታ የመፍጠር ኃላፊነት፣

3. ከባለሀብቱ ጋር የሚኖረን ተግባቦት በተነፃፃሪ ነፃ፣ ገለልተኛና መርህን መሰረት ማድረግ፤

4. በማንኛውም መልኩ ከባለሀብቶች ጋር ያልተገባ የግል ጥቅም ትስስር መፍጠር ፈጽሞ የተከለከለ ነው፤

5. የግል ዘርፉን አዎንታዊ ሀገራዊ አስተዋጽኦና እንቅስቃሴ ከሚገድቡ አመለካከትና ተግባራት የመቆጠብ ግዴታ

6. አባሉ እራሱ ባለሀብት በሚሆንበት ወቅት ህግና ሥርዓትን አክብሮ ግንባር ቀደምና አርዓያ ሆኖ የመንቀሳቀስ ግዴታ አለበት፡፡.

*"ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!"*

# (11) ከተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር የሚኖር ግንኙነት

1. ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ጋር የሚደረግ ግንኙነት በትብብር እና በፉክክር መካከል ሚዛን የጠበቀ እንዲሆን የማድረግ፤

2. በሀገራችን የመግባባት ዴሞክራሲን (Consociational Democracy) ለማጎልበት እንቅፋት ከሆኑ ድርጊቶች የመቆጠብ፤

3. ተፎካካሪ ፓርቲዎች በሀገሪቱ ህጎች መሰረት የፖለቲካ ስራ የመስራት መብታቸውን የሚገድብ ድርጊት ያለመፈጸም፤

4. በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚኖርን አቋም በግልጽ ተገንዝቦ ዴሞክራሲያዊ የሃሳብ ትግል በማድረግ ህብረተሰቡ ልዩነቶችን እንዲገነዘብ ማድረግ፤

5. ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር ዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ ግንኙነት መፍጠር፤ ልዩነቶችን በውይይትና በሰለጠነ በሃሳብ ትግል መመፍታት፤

6. መርህ አልባ እና ህገ ወጥ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ህግና ሥርዓትን በጠበቀ መልኩ የመታገል ኃላፊነት፡፡

*"ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!"*

# 12) የህግ የበላይነትን ከማስከበር አኳያ የሚኖሩ ግዴታዎች፣

1. አንድ የብልጽግና አባልና አመራር የፍትህና ዳኝነት ተቋማት ነጻና ገለልተኛ መሆናቸውን አምኖ መቀበል አለበት፡፡

2. የፍትህና ዳኝነት ተቋማት ስራዎቻቸውን በተገቢው መልኩ እየተወጡ ስለመሆናቸው ክትትልና ድጋፍ የማድረግ ኃላፊነት፣

3. የፍትህና ዳኝነት ተቋማት ለህብረተሰቡ ተገቢውን አገልግሎት መስጠት አለመቻላቸው ሲረጋገጥ ተጠያቂ የሚሆኑበትን ሁኔታ የመፍጠር ኃላፊነት አለበት፡፡

*"ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!"*

# 13) የኮሙዩኒኬሽንና የሚዲያ አጠቃቀም ግዴታዎች፤

1. በእቅድና በብቃት የመጠቀም፣ የፓርቲውን ስኬቶች ለሕዝብ የማስገንዘብና አፍራሽ ፕሮፓጋንዳን የመመከት.

2. የሚዲያ ተቋማትን የመተባበርና መረጃ የመስጠት ግዴታ፣

3. ሚዲያ ነጻና ገለልተኛ ለህዝብ ጥቅም የተቋቋመ ተቋም መሆኑን የማክበር ግዴታ፤

4. በሚዲያ የሚተላለፍ መልዕክት/መድረኮች በቂ ዝግጅት አድርጎ መልዕክቶችን በጥንቃቄ የማስተላለፍ ግዴታ፤

5. በሚዲያ የሚተላለፉ መልዕክቶች የፓርቲ መርሆዎች፣ እሴቶች፣ እቅዶችና አቋሞች ላይ የተመሰረቱ፣ ከሕዝቡ መልካም ባህልና እሴቶች ጋር የማይቃረኑ፣ የትስስር ትርክትን መሰረት ያደረጉና የሁሉም ኢትዮጵያዊያን የወል እውነት ለማጽናት የሚረዱ፤

6. ሕዝብን ከሕዝብ የሚያጋጩ እንዲሁም በሕዝቦች መካከል ጥርጣሬ የሚያጭሩ መልዕክቶችን ማስተላለፋ ሲረጋገጥ ተጠያቂ ይደረጋል፡፡

# . . . ኮሙዩኒኬሽንና የሚዲያ

7. ሚዲያዎችን ተጠቅሞ የግለሰቦችን ስም በመጥቀስ ወይም አከባቢን ጠቅሶ የሚወንጀል መልዕክት ካስተላለፈ በፓርቲው ደንብና አሰራር መሰረት እንዲሁም በወንጀል ተጠያቂ ይደረጋል፡፡

8. የሚዲያ አመራሮችን/ባለሙያዎችን መርህንና ተጨባጭ አፈፃፀምን ወይም ተግባርን መሰረት ባላደረገ መልኩ አለአግባብ ከሃላፊነታቸው እንዲነሱ ማድረግ፣ ማስፈራራት ወይም ዛቻ ማቅረብ፤

9. በማህበራዊ ሚዲያዎች እርስ በእርስ ወዳጅነት የመፍጠርና ሀሳብ የመጋራት መብት አለው፤ ከዚህ ውጪ ከፓርቲው መርሆዎች፣ እሴቶችና አሰራሮች ውጭ አሉታዊ በሆነ መልኩ አለመጠቀም፡፡

*"ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!"*

# ክፍል 4፡ የሥነ-ምግባር ጥሰቶች እና የእርምጃ አወሳሰድ(#14-24)




1. **የሥነ-ምግባር ጥሰቶች**
2. **የእርምጃ አወሳሰድ ሥነ ሥርዓት**
3. **የእርምጃ ዓይነቶች/እርከኖች (#6)**
4. **ቅጣትን የሚያከብዱ ሁኔታዎች**
5. **ቅጣትን የሚያቀሉ ሁኔታዎች**

***"ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!"***

# አንቀጽ 14 - የሥነ-ምግባር ጥሰቶች(#13)

1) የሀገሪቱን ሕገ መንግስትና ሌሎች ህጎች፣ የመንግስት ውሳኔዎችን አለማክበር፣

4) ያልተገባ ጥቅምና ክብር ለማግኘት ከሌሎች አካላት ጋር መርህ አልባ ግንኙነት መፍጠር፣

2) የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ፣ የአሰራር ስርዓቶች፣ መርሆዎች፣ እሴቶች፣ አቋሞችና ውሳኔዎች አለማክበር፣

5) የውስጠ ፓርቲው ዴሞክራሲ፣ አንድነት፣ ጥራትና ጥንካሬ በሚጎዱ ድርጊቶች ላይ መሰማራት፣

3) በፓርቲ የሚሰጡ ተልዕኮዎችና ስምሪቶችን አለመቀበል፣ ግዴታዎችን አለመፈፀም፣

6) የፓርቲውን ሕልውና አደጋ ላይ የሚጥል ተግባር መፈፀም፣

*"ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!"*

# . . . የሥነ-ምግባር ጥሰቶች

7) የአባላትን አንድነት ማላላት፣ መከፋፈል እና እርስ በርሳቸው በጥርጣሬ እንዲተያዩ ማድረግ፤

10) በሀሰት መረጃ አመራር/አባል መገምገም፣ ርምጃ እንዲወሰድት ማድረግ፣ ያለ ግብራቸዉ መልካም ስማቸዉን ማጠልሸት፤

8) የፓርቲውን ሚስጢር ላልተፈቀደለት ሰው ወይም አካል ማጋራት፣

11) ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ላይ መሳተፍ፤ ማገዝ፤ ማደፋፈር፤ ተባባሪ መሆን፤ ሽፋን መስጠት፣

9) ፓርቲውን ማጭበርበር፣ የሃሰት ሪፖርት ማቅረብ፤ በማህበራዊ ሚዲያ የሃሰት መረጃ፣ ማሰራጨት፣

12) ከህብረተሰቡ መልካም ባህል፣ እሴት፣ ልማድና ወግ ያፈነገጠ ድርጊት መከወን/ተባባሪ ሆኖ መገኘት፣

13. በመ/ደንብና ሌሎች መመሪያዎች ላይ የተቀመጡ ኃላፊነቶችና ግዴታዎች አለመወጣት፤

# አንቀጽ 15 - የሥነ-ምግባር ጥሰት እርምጃ አወሳሰድ ሥነ ሥርዓት(#9)

1. አባል/አመራር የሚታረመው በመድረኮች እና ስልጣን በተሰጠው የፓርቲው አካል ነው፡፡

2. አባል/አመራር ሂስ/መረጃ/ማስረጃ ማቅረብ ይችላል

3. ቅጣት በአባላት አብላጫ ድምጽ ከጸደቀ ተጠሪ ለሆነለት አካል እና አካል በማቅረብ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

4. የዲሲፕሊን ጥሰት ክስ የቀረበበት አባል/አመራር ምላሽ ከሰጠ በኃላ ውሳኔ ሊሰጥ ይገባል፤ ይኸው በመዝገብ መስፈር አለበት(5-6)፤

*"ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!"*

# . . . እርምጃ አወሳሰድ ሥነ ሥርዓት

5

የዲሲፕሊን ክስ ተደራጅቶ ለሚወስነው አካል የሚቀርበው በአደረጃጀት ዘርፍ አማካይነት ነው፡፡

6

የአደረጃጀት ዘርፍ የዲስፒሊን ክስ አጣርቶ የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ የዲሲፕሊን ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡

7

በሚሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ካለው በየደረጃው ለሚገኝ *የፓርቲ አደረጃጀት ቅሬታ አቅርቦ* በሚሰጠው ውሳኔ ካልረካ በየደረጃው ለሚገኘው *የኮሚሽን መዋቅር አቤቱታውን* የማቅረብና መልስ የማግኘት መብት አለው፤

*"ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!"*

# አንቀጽ 16 - ተግሳፅ የሚያሰጡ የሥነ-ምግባር ጥፋቶች(#5)

1. የፓርቲውን ተልዕኮ በተሟላ መልኩ በውጤታማነት አለመፈፀም፣

2. የህዋስ ወይም የመሰረታዊ ድርጅት መደበኛ የውይይት ፕሮግራም ላይ ያለ በቂ ምክንያት ለአንድ ጊዜ አለመገኘት፣

3. በግል ማህበራዊ ድረ-ገፅ ከፍተኛ ጉዳት የማያደርሱ የተሳሳተ መረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ ያጋራ፣

4. የፓርቲውን አባል ወይም አመራር ተገቢ ያልሆኑ ቃላትን በመጠቀም ለመጀመሪያ ጊዜ መናገር፣ .

5. ያለበቂ ምክንያት የአባላት ወርሃዊ ክፍያ ለአንድ ወር አለመክፈል፡፡

*"ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!"*

# አንቀጽ 17 - የቃል ማስጠንቀቂያ የሚያሰጡ ጥፋቶች(#13)

01 የፓርቲውን ተልዕኮ በመፈፀም ረገድ የፍቃደኛነትና የዝግጁነት ማነስ የታየበት ከሆነ፣ .

02 ልዩነቶችን በፀረ-ዴሞክራሲያዊ መንገድ ለመጀመሪያ ጊዜ ለመፍታት መሞከር፣

03 ከፓርቲዉ መተዳደሪያ ደንብና መመሪያ ዉጭ የአባላት ምልመላ ማከናወን፣

04 ከፍተኛ ጉዳት የማያደርስ አሉባልታ ለመጀመሪያ ጊዜ መንዛት፣

05 በህዋስ ወይም በመሠረታዊ ድርጅት መደበኛ የውይይት ፕሮግራም ያለበቂ ምክንያት በተከታታይ ለሁለት ጊዜ አለመገኘት፣

06. የፓርቲ እና የመንግስት የሥራ ሰዓት ያለማክበር፣

# … የቃል ማስጠንቀቂያ

በስራው ላይ ተገቢ ጥረትና ትጋት አለማሳየት

12. ስላከናወናቸው ሥራዎች ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ሪፖርት ያለማድረግ

የሐሰት ሪፖርትና የተዛባ መረጃን ሳያጣሩ ማስተላለፍ

07

09

10

11

08

በአገሪቱ ህግ መሰረት በወቅቱ ሀብት አለማስመዝገብ

ከስራ ባልደረገቦች ጋር ተባብሮ አለመስራትና እንቅፋት መሆን

በስራው ላይ ውጤታማ አለመሆንና ሂስ ተደርጎ አለማታረም

13. ወርሃዊ የአባልነት ክፍያ ያለበቂ ምክንያት ለሁለት ተከታታይ ወራት አለመክፈል፡፡

# አንቀጽ 18 - የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ የሚያሰጡ ጥፋቶች(#13)

1) ከፓርቲው ዓላማና ፕሮግራም ጋር የሚቃረን አቋም ሆን ብሎ ለአንድ ጊዜ ማንፀበራቅ

2) በአባልና ህዝብ መካከል *ሀብረ-ብሔራዊ ወንድማማችነት/እህትማማችነት እና አገራዊ አንድነት* እንዳይጠናከር እንቅፋት የሚሆኑ ሐሳቦችን በይፋ ለአንድ ጊዜ ማንፀበራቅ፣ .

3) የፓርቲውን አባል ወይም አመራር ተገቢ ያልሆኑ ቃላትን በመጠቀም ለሁለተኛ ጊዜ ማሸማቀቅ፣

4) ፓርቲው የሚያጋጥመውን ፓለቲካዊ ፈተና በፅናት ከመጋፈጥና ከመታገል ይልቅ የወላዋይነት አቋም መያዝ፤

5) ከፓርቲ መርህ ውጭ የሆኑ ወይም የፓርቲ አቋም ያልሆኑ ጉዳዮችን ለአንድ ጊዜ በማንኛውም ሚዲያ ማሰራጨት

*"ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!"*

# . . . የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ የሚያሰጡ

6) በፓርቲ ስራዎችና በመንግስት ስራዎች ላይ ዝቅተኛ አፈጻጸም ያስመዘገበ ወይም ለተከታታይ ሁለት የምዘና ዙሮች መካከለኛ አፈጻጸም ያስመዘገበ፣

7) ፓርቲው በመደበው ቦታ እና የሥራ ዘርፍ ያለበቂ ምክንያት ለማገልገል ፍቃደኛ አለመሆን፣

8) ከብልጽግና ፓርቲ መርህ ውጪ አዳዲስ አባላትን መደለያ በመስጠት ወይም በመቀበል ምልመላ ያደረገ፣

9) በሀሰት/በፈጠራ/ ሀሳብና በሀሰት መረጃ የፓርቲዉን መሪዎችና አባላት መገምገምና እርምጃ እንዲወሰድባቸዉ ማድረግና ያለ ግብራቸዉ መልካም ስማቸዉን ለማጠልሸት መሞከር፣



10) ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ሲፈጸሙ እያዩ እርምት እንዲደረግ አለማድረግ ወይም አለመታገል፣

11) የህዋስ ወይም የመሰረታዊ ድርጅት መደበኛ የውይይት ፕሮግራም ላይ ያለ በቂ ምክንያት በተከታታይ ከሶስት ጊዜ በላይ አለመገኘት፣

12) ያለበቂ ምክንያት የአባልነት ወርሃዊ ክፍያ ለአራት ተከታታይ ወራት አለመክፈል፣

13) በስራ ቦታና በህብረተሰቡ ውስጥ ለሞራል፣ ለመልካም ሥነ-ምግባርና ለእሴት ተቃራኒ የሆነ ድርጊት መፈጸም፣

*“ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!”*

# አንቀጽ 19 - ከኃላፊነት የሚያስነሱ የስነ-ምግባር ጥፋቶች(#14)

1) የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ፣ እሴት፣ መመሪያ እና ውሳኔ አለማክበር፤ በዚህም በፓርቲዉ ህልዉና እና ዓላማዎች ከፍተኛ አሉታዊ ተጽእኖ መፍጠር፣

2) ከፓርቲው ዓላማና ፕሮግራም ጋር የሚቃረን አቋም በይፋ ከአንድ ጊዜ በላይ ማንፀባረቅ፣

3) ህብረ-ብሔራዊ ወንድማማችነት/እህትማማችነትን እና አገራዊ አንድነትን በከፍተኛ ደረጃ የሚጎዳ ድርጊት መፈፀም ወይም መጠነኛ ጉዳት የሚያደርሱ ድርጊቶችን በተደጋጋሚ መፈፀምና ስህተትን ለማረም ዝግጁ አለመሆን፣

4) በፓርቲው የተሰጠውን ኃላፊነትና ተልዕኮ በብቃት አለመወጣት እና በጽሁፍ ማስጠንቀቂያም ተሰጥቶት አለማስተካከል፣ .

5) የሕዝብን ደህንነትና የአገርን ሉዓላዊነት አደጋ ላይ የሚጥል አመለካከት መያዝ፤ ይህንኑ አመለካከት በተግባር አንፀባርቆ መገኘት፣

"ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ

# . . . ከኃላፊነት የሚያስነሱ

6) ጉቦ መቀበል ወይም እንዲሰጠው መጠየቅ፣ ሙስና መፈፀም፣ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራስ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት መስራት፣

7) በአገሪቱ ህግ መሰረት በትክክል ሀብት ለማስመዝገብ ዝግጁ አለመሆን፣

8) የቡድን መንፈስን በመጠበቅ ከሥራ ባልደረቦች ጋር ተግባብቶ ተልዕኮን ለመፈፀም አለመቻል፤ ፀረ-ዲሞክራሲያዊ የሆኑ ተግባራትን በተደጋጋሚ መፈፀም፣ የፓርቲውን አባል ወይም አመራር ተገቢ ያልሆኑ ቃላትን በመጠቀም ሁለት ጊዜ በላይ ማሸማቀቅ፣

9) በፓርቲው ሕልውና ላይ አደጋ በሚጋርጥ የአንጃነትና የቡድንተኛ እንቅስቃሴ መሣተፍና የቡድንተኝነት አስተሳሰብን ማራመድ፣

10) የፓርቲን ተልዕኮና የጋራ ውሳኔዎች በጠበቀ ሁኔታ ከላይ ወደታች የሚተላለፉ ውሳኔዎችን ከመፈፀምና የሥራ አቅጣጫዎችን ከመከተል ይልቅ የግል ፍላጎትን ማዕከል አድርጎ በመንቀሳቀስ በፓርቲ ላይ ጉዳት ማስከተል፣ .

“ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!

# . . . ከኃላፊነት የሚያስነሱ

11) በተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች መካከል ግጭት ሊያስከትል የሚችል ወይም ሀገርንና ፓርቲውን በከፍተኛ ደረጃ የሚጎዳ መልእክት በማህበራዊ እና በመደበኛ ሚዲያዎች ማሰራጨት ወይም ማጋራት፣

12) በሀሰት/በፈጠራ/ እና በሀሰት መረጃ የፓርቲዉን አመራሮችና አባላት መገምገም፣ መመዘንና እርምጃ እንዲወሰድባቸዉ ማድረግና ያለ ግብራቸዉ መልካም ስማቸዉን ለማጠልሸት መሞከር እና እንዲያስተካክል ቢገለጽለትም ማስተካከል አለመፈለግ፣

13) አመራር እና አባላትን ለመጉዳት፣ እርምጃ ለማስወሰድ ወይም ለማጥቃት በማሰብ ሀሰት በመፍጠርም ሆነ እዉነታን በማዛባት ስልጣንን በመጠቀም አመራሮችና አባላት ላይ ማደራጀት እና መደራጀት፣

14) የሐሰት ሪፖርት ከአንድ ጊዜ በላይ ማስተላለፍ፣

"ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!"

# አንቀጽ 20 - ከኃላፊነትና አባልነት ስለማገድ(#4)

1) አመራሩ በኃላፊነት መቆየቱ ችግር ያስከትላል ተብሎ ሲታመንበት ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ከ3 ወር ባልበለጠ ጊዜ የሾመው/የመደበው አካል ወይም ስልጣን የተሰጠው አካል ከኃላፊነት ታግዶ እንዲቆይ ያደርጋል፡፡

2) አንድ አባል ክስ የቀረበበት እንደሆነ የተደራጀበት መሰረታዊ ድርጅት ወይም ከፍ ብለው ያሉ የፓርቲው አካላት ጉዳዩን አይተው ውሳኔ እስከሚሰጡ ድረስ ከሁለት ወር ላልበለጠ ጊዜ አባሉን ከአባልነት አግደው ለማቆየት ይችላሉ፡፡

3) በተወሰነው ጊዜ ገደብ ውስጥ ተፈጽሟል የተባለውን የዲስፐሊን ጥፋት አጣርቶ ለውሳኔ ማብቃት ያልተቻለ እንደሆነ ለተጨማሪ 15 የስራ ቀናት ብቻ ማራዘም ይቻላል፡፡

4) የታገደው አመራር ውሳኔ እስኪሰጠው ድረስ በህግ አግባብ ደመወዙ ሊከፈለው ይችላል፡፡

*"ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!"*

# አንቀጽ 21-ከአባልነት የሚያሰርዙ የሥነ-ምግባር ግድፈቶች/ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋቶች(#15)

1) ሕብረ ብሔራዊ ወንድማማችነትንና አገራዊ አንድነትን በተመለከተ ፓርቲው ከያዘው አቋም የተለየ አቋም ማራመድና ይህንኑ በተግባር መግለፅ፣

2) የሃሰት ሪፖርት ማቅረብ፤ ፓርቲውን ለማጭበርበር መሞከር፣ ሃሰተኛ መረጃዎችንና መግለጫዎችን በማህበራዊ ሚዲያ እና ሌሎች ሚዲያዎች ማሰራጨት፣

3) ከፓርቲ የተሰጠን ኃላፊነት የግል ጥቅም ማካበቻ ማድረግ፤ በሙስናና ብልሹ አሰራር ውስጥ መገኘት፤ በራስ/በሌላ አባል ላይ የተጀመረን የዲሲፕሊን ክስ ምርመራን ለማደናቀፍ መሞከር፣

4) የፓርቲውን ሕልውና አደጋ ውስጥ ለመጣል በአንጀኝነትና በቡድንተኝነት መንቀሳቀስ፤

5) ብሔርን፣ ሃይማኖትን፣ የኑሮ ደረጃን ወይም ሌላ ማህበራዊ መለያን መሠረት በማድረግ የፓርቲ አባላት የአስተሳሰብና የተግባር አንድነት እንዳይኖራቸው እና እንዲከፋፈሉ ማድረግ፣

6) በየእርከኑ ወይም በየደረጃው በሚገኘው የፓርቲ መዋቅር የሚደረጉ ስብሰባዎች ምልዓተ ጉባኤ እንዳይሟላ በማሰብ ሆነ ብሎ በተደጋጋሚ ከስብሰባ መቅረትና ሌሎች እንዳይገኙ ማድረግ፣

# . . .ከአባልነት የሚያሰርዙ

7) ፈተናዎችን በፅናት ከመጋፈጥ ይልቅ ማምለጫ መንገዶችን ለግል ጥቅሙ ብቻ በማሰብ መንቀሳቀስ፣

8) መርህ አልባ በሆነ መንገድ የተወሰኑ አካላትን ድጋፍ ለማግኘትና በህዝበኝነት በሕዝቦች መካከል ጥርጣሬና ግጭት ሊፈጥር የሚችል ስሜት ኮርኳሪ ንግግር ማድረግ ወይም በማህበራዊ ሚዲያ አልያም በማንኛዉም ሚዲያ ማጋራት፣

9) ፓርቲው በሚያስተላልፋቸው ውሳኔዎች ላይ በግል የተያዙ አቋሞችን የቡድን ወይም አጠቃላይ የፓርቲው አቋም አድርጎ ማቅረብና ማሰራጨት፣

10) የሌላ የፖለቲካ ፓርቲ አባል ሆኖ መገኘት፣

11) በፍርድ ቤት በሚሰጥ ውሳኔ የመደራጀት /ሲቪልና የፖለቲካ መብቱ/ መገፈፍ፣

12) የፓርቲውን ድረ ገፆች፣ የዜና አውታሮች እና ልዩ ልዩ ሚዲያዎችን በመጠቀም ፓርቲው በሕዝቡ ዘንድ ተአማኒነትና ተቀባይነት እንዳይኖረው መስራት፣

13) ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ አለመሆኑ ሲረጋገጥ፣

14) በቂ ባልሆነ ምክንያት ወርሃዊ የአባልነት ክፍያን ለስድስት ተከታታይ ወራት አለመክፈል፣

15) ሰርጎ ገብ ሆኖ በፓርቲ አባልነት ሽፋን ልዩ ተልዕኮ ይዞ መንቀሳቀስና የሌላ አካል ዓላማ አስፈፃሚ መሆን፡፡

# አንቀጽ 22 - ከአባልነት የተሰናበተ አባል ተመልሶ አባል የሚደረግበት ሁኔታ

1) ከአባልነት የተሰናበተ ሰው ውሳኔው ከተላለፈ ከአንድ አመት በኃላ በጥፋቱ መጸጸቱንና መሻሻል ማሳየቱን ገልፆ ወደ አባልነት ለመመለስ በጽሑፍ የዲስፕሊን እርምጃ ለወሰደበት አካል ሊያቀርብ ይችላል፡፡

A

B

C

D

2) የዳግም አባል ልሁን ጥያቄ ሊቀርብ የሚገባዉ በዲስፕሊን እርምጃ ተወስዶበት ከአባልነት ተሰናብቶ በነበረዉ ግለሰብ በራሱ ሲሆን የመመለስ ጥያቄዉን በጥፋቱ መጸጸቱንና የጸባይና የተግባር መሻሻል ስለማድረጉ የሚያሳምኑ መረጃዎችን በማከል ማቅረብ ይኖርበታል፣

3) የዳግም አባልነት ጥያቄ የቀረበለት ቀድሞ ውሳኔ ያስተላለፈ አካል አጣርቶ በ ¾ ድምጽ ያፀደቀ እንደሆነ የውሳኔ ሐሳቡን አንድ ደረጃ ከፍ ላለ የፓርቲው አካል ያቀርባል፣

4) ከዚያም የውሳኔ ሐሳብ የቀረበለት አካል የውሳኔ ሐሳቡን ከመረመረ በኃላ አግባብነት ያለው ሆኖ ካገኘው የዳግም አባልነት ጥያቄውን በ3/4 ድምጽ ያጸድቃል፣

*"ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!"*

# . . . ተመልሶ አባል ስለመሆን

5) ቀድሞ የዲስፕሊን ቅጣት ያስተላለፈበት መዋቅር ጋር በስራም ሆነ በመኖሪያ አካባቢ እንደማይገናኝ ከተረጋገጠ አሁን በሚሰራበት/በሚኖርበት አካባቢ ባለች መሰረታዊ ድርጅት ጥያቄዉን ሊያቀርብ ይችላል፣

6) የዳግም አባልነት ጥያቄዉ የቀረበለት መዋቅር ቀድሞ ከአባልነት ያሰናበተዉ መዋቅር ሳይሆን ግለሰቡ አሁን በስራ/በመኖሪያ ቀይሮ የመጣበት መዋቅር በሚሆንበት ጊዜ ቀድሞ ከአባልነት የመሰናበት ዉሳኔ ካስተላለፈበት መዋቅር ላይ የዉሳኔዎችን ዶክመንቶች ኮፒ በመቀበል ለቀረበለት ጥያቄ ምርመራ እንደዋና መነሻ አድርጎ መጠቀም ይኖርበታል፣

7) አንድን አመራር ወይም አባል በምንም መልኩ ከአንድ ዓመት በታች መመለስ ፈጽሞ የተከለከለ ነው፡፡

G

E

F

"ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!"

# አንቀጽ 23 - ቅጣትን የሚያከብዱ ሁኔታዎች

1) ክስ የቀረበበትን ጥፋት በተደጋጋሚ መፈፀም፣

2) በጥፋት አለመፀፀትና ይህንኑ በተግባር ለመግለፅ አለመቻል፡፡

*"ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!"*

## አንቀጽ 24 - ቅጣትን የሚያቀሉ ሁኔታዎች

1) ጥፋትን ማመን፣ መፀፀትና ይህንኑ በተግባር መግለፅ፣

2) መልካም ሥነ-ምግባር ያለው ለመሆኑ በሌሎች አባላት የሚሰጥ ምስክርነት፣

3) በተሰማራበት መስክ መልካም የሥራ አፈፃፀም የነበረው መሆኑ

4)ጥፋት የፈፀመው ለመጀመሪያ ጊዜ መሆን

5) ለማህበረሰቡ ከፍ ያለ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት የፈፀመ መሆን፡፡



*"ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!"*

# ክፍል 5፡ የቅሬታና አቤቱታ አቀራረብና አፈታት የአሰራር ስርዓት(#25-31)




1. የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት
2. ለኮሚሽኑ የአቤቱታ አቀራረብ ሥርዓት
3. የሥነ-ምግባር ክስ፣ የውሳኔ አሰጣጥና ቅሬታ አቀራረብ
4. የቅሬታ ወይም አቤቱታ የማጣራት ሥርዓት
5. የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት
6. የውሳኔ አሰጣጥ ይዘት
7. የቅጣት ውሳኔ ስለማሳወቅ

# አንቀጽ 25 - የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት

1) ማንኛውም አባል ወይም አመራር አድሎ ተፈጸመብኝ ብሎ ካመነ ቅሬታውን ከህዋስ - ፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ድረስ ማቅረብ ይችላል፣

2) በየደረጃው የሚቀረብው ቅሬታ ከታችኛው የፓርቲ አካል ውሳኔ የተሰጠው ጉዳይ ቀጥሎ ላለው አካል መቅረብ ይኖርበታል፣

3) ቅሬታ በፅሁፍ ሆኖ የቅሬታ አቅራቢው ሙሉ ስም፣ የቅሬታ ጭብጥ፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ ውሳኔ የተሰጠው እንደሆነ ከውሳኔው ጋር በፊርማ ተደግፎ መቅረብ ይኖርበታል፣

ማንኛውም ቅሬታ አቅራቢ ለቅሬታው መነሻ የሆነ ውሳኔ ወይም ድርጊት ከተፈፀመበት ጊዜ አንስቶ ባሉት ተከታታይ ቀናት:-

ለመሠረታዊ ድርጅት በአንድ ወር ውስጥ፣

የቀበሌ /መሰረታዊ ድርጅት/ ከወሰነበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ውስጥ ለወረዳ ወይም በወረዳ ደረጃ ላሉ ከተሞች ጽ/ቤት፣

የወረዳ ፓርቲ ቅ/ጽ/ቤት ከወሰነበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ውስጥ ለዞን ወይም በዞን ደረጃ ላሉ ከተሞችና ክፍለ ከተሞች ጽ/ቤት፣

የዞን ፓርቲ ቅ/ጽ/ቤት ከወሰነበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ውስጥ ለክልል ፓርቲ ቅ/ጽ/ቤት

የክልል ፓርቲ ቅ/ጽ/ቤት ከወሰነበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ውስጥ ለፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ካልቀረበ በይርጋ የታገደ ይሆናል፣

ቅሬታ የቀረበለት የፓርቲ መዋቅር ቅሬታው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ምላሹን በጽሑፍ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

# አንቀጽ 26 - ለኮሚሽኑ የአቤቱታ አቀራረብ ሥርዓት

1) ማንኛውም የፓርቲው አባላት ከፓርቲው መተዳደርያ ደንብና መመሪያዎች ውጭ ርምጃ ተወስዶብኛል ወይም አድልኦ ተፈጽሞኛል ብሎ ካመነ አቤቱታውን በየደረጃው ላለው ኮሚሽን ማቅረብ ይችላል፣

2) የሚቀርበው አቤቱታ በየደረጃው ላለው የፓርቲ መዋቅር አቅርቦ በውሳኔው ካልረካ ብቻ ይሆናል፣

3) በየደረጃው ለኮሚሽኑ የሚቀርበው አቤቱታ በፅሁፍ ሆኖ የአቤቱታ አቅራቢው ሙሉ ስም፣ የአቤቱታ ጭብጥ፣ የውሳኔ ግልባጭ እና ሌሎች ደጋፊ ማስረጃዎች ጋር በፊርማ ተደግፎ መቅረብ ይኖርበታል፣

4) ማንኛውም አቤቱታ አቅራቢ የሚመለከተው አካል ለአቤቱታው መነሻ የሆነ ውሳኔ ከሰጠበት ጊዜ አንስቶ ባሉት ተከታታይ ሶስት ወራት ውስጥ ማቅረብ ይኖርበታል፣ በሶስት ወር ውስጥ ካልቀረበ አቤቱታ በይርጋ የታገደ ይሆናል፡፡

*"ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!"*

# አንቀጽ 27 - የሥነ-ምግባር ክስ፣ የውሳኔ አሰጣጥና ቅሬታ አቀራረብ

## 1) ለማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት፡-

ሀ) የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል የዲሲፕሊን ጥፋት ክስ የሚታየው በማዕከላዊ ኮሚቴው ነው፡፡ ክሱ ለማዕከላዊ ኮሚቴ የሚቀርበውም በፓርቲው ዋና ጽ/ቤት አማካይነት ይሆናል፡፡

ለ) ማዕከላዊ ኮሚቴው የቀረበለትን ክስ በዚህ መመሪያ መሠረት ከመረመረ በኋላ የራሱን ውሳኔ ያሳርፍበትና ለጉባኤው ያቀርባል፡፡

ሐ) ጉባኤው በማዕከላዊ ኮሚቴ የቀረበለትን የውሳኔ ሃሳብ ሊያፀድቅ ወይም ሊሽር ይችላል፡፡ የጉባኤው ውሳኔ ይግባኝ የማይባልበት የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል፡፡

መ) ክስ የቀረበበት የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ማዕከላዊ ኮሚቴው ለጉባኤው በሚያቀርበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ቅሬታ ካለው *ለጉባኤዉ ከመቅረቡ አስቀድሞ ቅሬታውን ለኢንስፔክሽንና ሥነ-ምግባር ኮሚሽን ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ኮሚሽኑ የማዕከላዊ ኮሚቴውን የውሳኔ ሃሳብ የሻረው እንደሆነ* የውሳኔ ሃሳቡ ውድቅ ይሆናል፣ ለጉባኤም አይቀርብም፡፡

ሠ) ማዕከላዊ ኮሚቴው ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ በኮሚሽኑ ዘንድ ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ፣ ጉባኤው ተከሳሹ በአካል ተገኝቶ ሃሳቡን እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡ ጉባኤው ተከሳሹን ካዳመጠ በኋላ ውይይት አድርጎ ይግባኝ የማይጠየቅበት የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## 2) የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ያልሆኑ አባላትና አመራሮች ፡-

ሀ) የአመራሮችና አባላት የዲሲፕሊን ጥፋት ክስ የሚቀርበው አባል በሆነበት መዋቅር ወይም አባሉን በቅርበት የመከታተል ኃላፊነት ያለበት አመራር ወይም እውነተኛ መረጃና ማስረጃ ባለው ማንኛውም አባልና አመራር ሊሆን ይችላል፡፡

ለ) በአመራር ወይም አባል ላይ የቀረበው ክስ የሚታየው አባሉ በታቀፈበት የፓርቲ አደረጃጀት ይሆናል፡፡

ሐ) በአደረጃጀቱ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው አመራር ወይም አባል ለትዩዩ ኢንስፔክሽንና ስነ ምግባር ኮሚሽን ቅሬታዉን ማቅረብ ይችላል፡፡

መ) በአቤቱታ በቀረበለት ኮሚሽን ምላሽ ያልተስማማ አመራር ወይም አባል አቤቱታውን አንድ እርከን ከፍ ላለ የኮሚሽኑ አካል አቤቱታውን ሊያቀርብ ይችላል፡፡


ሠ) ይግባኝ ስለማቅረብ፡-

- በወረዳ ደረጃ ላሉት እና በይግባኝ ከቀበሌ/መሰረታዊ ድርጅት ለቀረበ አቤቱታ የወረዳ ኮሚሽን፣
- በዞን ደረጃ ላሉት እና በይግባኝ ከወረዳ ለቀረበ የዞን ኮሚሽን፣
- በክልል ደረጃ ላሉት እና በይግባኝ ከዞን ለቀረበ የክልል ኮሚሽን እና
- በፌዴራል ደረጃ ላሉት እና በይግባኝ ከክልል ለቀረበ የማዕከል ኮሚሽን የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል፡፡

### መ) የኢንስፔክሽንና ሥነ-ምግባር አመራርና አባላት፡-

- የኢንስፔክሽንና ስነ ምግባር ኮሚሽን አመራርና አባላት መመሪያ ቁጥር1/2014 በጸደቀው የኮሚሽኑ የአሰራርና አደረጃጀት መመሪያ ላይ በተቀመጠው የአሰራር ስርዓት መሰረት ተጠያቂ እንዲሆኑ የሚደረግ ይሆናል፡፡

# አንቀጽ 28 - የቅሬታ ወይም አቤቱታ የማጣራት ሥርዓት




1) የቀረቡትን ቅሬታዎች ወይም አቤቱታዎች ቅቡልነት እና በበቂ መረጃ የተደገፈ ስለመሆኑ ይጣራል፣ ያልተሟላ መረጃ ካለ እንዲሟላ መደረግ ይኖርበታል፣

2) ቅሬታ የቀረበለት የፓርቲ አካላት አጣሪ ኮሚቴ አዋቅሮ ቢበዛ በአንድ ወር ውስጥ ማጣራት ይኖርባቸዋል፣

3) ቅሬታ ለማጣራት የተቋቋመ የኮሚቴ አባላት የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብና መመሪያዎች መሰረት በማድረግ በገለልተኝነት ማጣራት ይኖርባቸዋል፣

4) በየደረጃው ለኮሚሽኑ የቀረቡ የአባላት አቤቱታ ከኮሚሽኑ አመራሮች ወይም አባላት ወይም በኮሚሽን ጽ/ቤት ሠራተኞች ተሰይመው ቢበዛ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መጣራት ይኖርበታል፣

5) የተጣራ አቤቱታ ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ ለኮሚሽኑ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

# አንቀጽ 29 - የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት

1) ከአባላት የሚቀርቡ ቅሬታዎች በአጣሪ ኮሚቴ ተጣርተው በየደረጃው ለሚገኙ የፓርቲ አመራር አካላት ቀርበው በዚህ መመሪያ መሰረት ውሳኔ መሰጠት ይኖርባቸዋል፣

2) የውሳኔ ሃሳብ የቀረበለት የፓርቲ የአመራር ኮሚቴ ተጨማሪ ማጣራት/አስረጂ አስቀርበው ማጣራት ይችላሉ፣

3) በየደረጃው ውሳኔ የሰጠው የፓርቲ አመራር አካል ውሳኔውን ለሚመለከታቸው የፓርቲ አካላት ሲልኩ፣ ለቅሬታ አቅራቢው የውሳኔውን ግልባጭ በጽሁፍ መስጠት ይኖርባቸዋል፣

4) በቀረበው ቅሬታ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ቢበዛ በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ለሚመለከታቸውና ለቅሬታ አቅራቢው እንዲያውቁት መደረግ ይኖርበታል፣

5) አቤቱታ ቀርቦለት ያጣራ ወይም የመረመረ *በየደረጃው የሚገኝ የኮሚሽኑ አካል* ውሳኔውን ከእርምት የውሳኔ ሐሳብ ጋር በየደረጃው ላሉ የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ ወይም አካላት *በጽሁፍ መስጠት* ይኖርባቸዋል፣

6) የኮሚሽኑ የእርምት የውሳኔ ሐሳብ ተቀባይነት ካላገኘ በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 23(10) መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

7) የኮሚሽኑ ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

# አንቀጽ 30 - የውሳኔ አሰጣጥ ይዘት

1) የቀረቡት የቅሬታ ወይም አቤቱታ ጭብጦች፣ የቀረቡ የውሳኔ ሐሳቦችና የተሰጡ ውሳኔዎች፣

2) የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ እና መመሪያዎች ድንጋጌዎች፣

3) ውሳኔው በየደረጃው በአካል የተወሰነ ስለመሆኑና ውሳኔውን በሰጡ አባላት መካከል ልዩነት ካለ የልዩነት ነጥብ የተገለጸ ስለመሆኑ


4) ውሳኔው ላይ የተገኙ አባላት የፈረሙበት ቃለ ጉባዔ መሆን ይኖርበታል፡፡



*“ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!”*

# አንቀጽ 31 - የቅጣት ውሳኔ ስለማሳወቅ

1) ማንኛውም አባል የተወሰደበትን የሥነ ምግባር እርምጃ ወይም የቅጣት ውሳኔ **በጽሑፍ የማግኘት መብት** አለው፣




2) የፓርቲው ዋና ጽ/ቤት በፓርቲው የተወሰደውን የሥነ ምግባር እርምጃ ወይም የቅጣት ውሳኔ ለተወሰደበት **የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል በጽሑፍ** ያሳውቃል፡፡

3) በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲ ጽ/ቤቶች በፓርቲው የተወሰደውን የሥነ ምግባር እርምጃ/የቅጣት ውሳኔ **ለተወሰደበት አመራር/አባል በጽሑፍ** ያሳውቃል፡፡

4) የፓርቲ ጽ/ቤቶች ለሥነ ምግባር እርምጃ/ለቅጣት ውሳኔ መነሻ የሆኑ **የግምገማና ምዘና ሰነዶችን በተጠየቁ** ጊዜ የማሳየት ግዴታ አለባቸው፡፡

# ክፍል 6 - ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 32) ስንብት ስለማጸደቅ

- አባሉ በተደራጀበት የፓርቲው አካል ውሳኔ ሐሳብ አቅራቢነት በመሠረታዊ ድርጅት ጠቅላላ አባላት ኮንፈረንስ ቀርቦ መፅደቅ አለበት፡፡

## 33) ስለመመዝገብ

- በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲ ጽ/ቤቶች የርምጃ መረጃውን በሃርድና ሶፍት ኮፒ መያዝ አለባቸው፡፡




## 34) ግንዛቤ ስለመፍጠር

- ኮሚሽኑ እና
- በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲ መዋቅሮች፤

## 35. የመተባበር ግዴታ

- ማንኛውም፡_
  - የፓርቲ አካላት፣
  - አመራርና
  - አባላት አለባቸው፡፡

*"ጠንካራ ኢንስፔክሽን፣ ለጠንካራ ፓርቲ!"*

# ቀጣይ ተግባራችን

1. የኮሚሽን አባላት፣ የጽ/ቤት ኃላፊዎችና ባለሙያዎች:-
    1. በተሻሻለው የኮሚሽኑ አደረጃጀትና አሰራር መመሪያ #2/2016፣
    2. የኮሚሽኑ የግምገማና ምዘና መመሪያ #3/2016፣
    3. የዲሲፕሊን መመሪያ እና
    4. የኮሚሽኑ የአቤቱታ አቀራረብና አፈታት መመሪያ #4/2016 ላይ ስልጠና መስጠት።
2. ለፓርቲ አመራርና አባላት ከአደረጃጀት ዘርፍ ጋር በመሆን:-
    1. በዲሲፕሊን መመሪያ እና
    2. *የኮሚሽኑ የአቤቱታ አቀራረብና አፈታት መመሪያ #4/2016 ላይ* ስልጠና መስጠት ይጠበቅብናል።

ብልፅግና ፓርቲ
PROSPERITY PARTY

# አመሠግናለሁ!

# Galatoomaa!

# Mahadsanid!

# የቐንየለይ!

# Gadda Ge!

# አሳሁ መገን!

# Galateemmo!

***Habtamu Sisay Hawas***
***Cell Phone: +251 911584564***
*Twitter - @HabtamuS_Awas*
*Telegram - @habtsis*
**E-mail - habtsis@yahoo.com**
*obsaa2000@gmail.com*
*P.O.Box: 13780(Private)*